የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ—ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 13
ADDIS ABABA - 3rd Feb., 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፺፭/፲፱፻፺ ዓ.ም.
በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ሙከራ ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ............................... ገጽ ፮፻፷፯

CONTENTS

Proclamation No. 95/1998
Convention for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income and the Prevention of Fiscal Evasion between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic Ratification Proclamation ............................. Page 667

**አዋጅ ቁጥር ፺፭/፲፱፻፺**
**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ሙከራ ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረትና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ሙከራ ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ.ኤ.አ. ኤፕሪል ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ በሮም የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

*PROCLAMATION NO.95/1998*
*A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRTIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ITALIAN REPUBLIC FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION*

WHEREAS, a Convention for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income and the Prevention of Fiscal Evasion was signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic in Rome on the 8th day of April, 1997;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said convention at its session held on the 3rd day of February, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

፩· አጭር ርዕስ

"ተደራራቢ የገቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረግን ሙከራ ለመከላከል ከኢጣሊያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፺፭/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ·ኤ·አ· ኤፕሪል ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ በሮም የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና ግብር ላለመክፈል የሚደረገውን ሙከራ ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት ጸድቋል።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Convention for the Avoidance of Double Taxation with Respect to taxes on Income and the prevention of Fiscal Evasion with the Government of the Italian Republic Ratification Proclamation No. 95/1998.".

2. *Ratification of the Convention*

The Convention between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic for the avoidance of Double Taxation with Respect to taxes on Income and the Prevention of Fiscal Evasion signed in Rome on the 8th day of April, 1997 is ratified.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned governmental organs.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 3rd day of February, 1998.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of February, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE